# ይድረስ ለቀድሞ የወያኔ አመራር ቡድን አባሎች

## የአቶ ስዩምና ወያኔዎች የ17 ዓመታት "የከሸፈ ዲፕሎማሲ ጉዞ"

**አክሱም ሆቴል**

**መቀሌ፡ ትግራይ ክልል ኢትዮጵያ**

ባድመ ለኛ ተወሰነ የሚለው የአቶ ስዩም መግለጫ ምንጩ ምንድን ነው? የአፍሪካዊው ዲፕሎማት ሚናስ ምንነበር?

### ግልጽ ድብዳቤ

<u>**ጉዳዩ፡-**</u> <u>በኤርትራና በንፁህ ኤርትራዊያን ላይ የፈፀማችሁትን ታሪካዊ ስህተቶችና ግፎችን ስለ ማስታወስ</u>

በቅድሚያ የኛ ባህል በሚጠይቀው ጨዋነት መሠረት ሰላምታዬን አስቀድማለሁ:: ከሥልጣን ከተባረራችሁና አራት ኪሎ ከሚገኘው ቤተ መንግሥት ጠቀልላችሁ ወጥታችሁ መቀሌ መመሸጋችሁን ከሰማሁ ሁለት ዓመት አልፎታል:: ሆኖም እስከዛሬ በትዕግስት ምንም ሳልል ቆይቼ አሁን ትዝ ያላችሁኝ ባለፉት ሦስት ወራት በትግራይ ቲቪና ድምፂ ወያኔ በተደጋጋሚ ብቅ እያላችሁ ኤርትራን በተመለከተ የምትሰጡትን መግለጫ ከተከታተልኩ በኋላ ነው:: ስለ ኤርትራ ብዙ ዐበይት ጉዳዮች አንስታችኋል::

የኤርትራ ሕዝብ ወንድማችሁ መሆኑንና የፈፀማችሁትን በደል ሕዝቡ እንዲረሳውና ወደ ቀድሞው ግንኙነትና በጎ ጉርብትና እንዲመለስ በተደጋጋሚ ጥሪያችሁን አቅርባችኋል:: እኔም በበኩሌ እንደ ኤርትራዊ እናንተ በንፁህ ኤርትራዊያን ላይ የፈጸማችሁትን ይቅር የማይባል ግፍ ለማስታወስ እና ታሪካዊ ክህደታችሁንም እንደማንረሳው ለማሳሰብ ይህን ግልጽ ደብዳቤ ለመጻፍ ተገድጄያለሁ:: የኛ የኤርትራዊያንን ብሶትና ቁጭት ግልፅ በሆነ ቋንቋ ለመግለፅ ስነሳ እናንተንም እያወቃችሁ ከገባችሁበት አውቆ የመርሳት በሽታ (selected memory loss syndrome) ለማላቀቅ ይረዳችኋል ብዬ አምናለሁ:: ይህን ሦስት ዐበይት ነጥቦችን የያዘውን ደብዳቤ የታሪክ ማስታወሻ እንዲሆናችሁ አድራሻውን በቀጥታ በናንተ ማድረጉን መርጫለሁ:: በሰላማዊውና ንፁህ ኤርትራዊያን ላይ የፈፀማችሁትን ግፍ የትግራይ ሕዝብ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ግንዛቤ እንዲያገኝበት በማሰብ የዚህ የጽሁፍ ቅጅ በዶ/ር ደብረጽዮን ገብረሚካኤል በኩል እንዲደርሳችሁ የእሳቸውን ትብብር እጠይቃለሁ::

### ክፍል አንድ፡-

የድንበር ኮሚሽን ስለ ባድመ የሰጠውን ውሳኔ ለ20 ዓመታት አንቀብለም በሚል በእምቢታችሁ መቀጠላችሁ::

**1.** አቶ ሥዩም መስፍን ለ18 ዓመታት በቆዩበት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ከፍተኛውን የዲፕሎማሲ ሥልጣን ተሸክመው እሳቸውና የቀድሞ የወያኔ ባለስልጣኖች ከዲፕሎማሲያዊ ብቃት አንጻር የነበራቸውን ጉድለት እና ክፍተት ሳከፈላችሁ:: ከ1998 እስከ 2000 (እ/ኤ/አ) ከተከሰተው የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በኋላ አቶ ስዩም መስፍን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከፍተኛውን የዲፕሎማሲ ሥልጣን ተሸክመው አልጀሪያ በተደረገው የሰላም ድርድር የኢትዮጵያ መንግሥትን ወክለው የአልጀርስን ስምምነት ፈረሙ፣ በዚሁም መሠረት የድንበር ችግሩ በድንበር ኮሚሽን ውሳኔ እንዲያገኝ በታህሳስ ወር 2000 በመሪዎች ደረጃ ሥምምነት ላይ ተደረሰ::

**2.** የድንበር ኮሚሽን ሁለቱም አገሮች በመረጧቸውና በተስማሙባቸው አምስት አባላት የዳኞች ቡድን ተሰየመ፡ ሁለቱም መንግሥታት (ኤርትራና ኢትዮጵያ) በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ታዋቂነት ባላቸው የሕግ ባለሙያዎች ያዋቀሩት የድንበር ኮሚሽን ሦስት መርህ አፀደቀ:: (ሀ) የሁለቱ አገሮች ድንበሮች በኢትዮጵያና ጣልያን መንግሥታት በ1900፣ 1902ና 1908 (ኤ.አ.አ) በተፈፀሙት የቅኝ ግዛት የድንበር ውሎች መሠረት ይሆናል:: (ለ) የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔውን ሲወስን በዓለም አቀፍ ሕግና በተጠቀሱት የቅኝ ግዛት ውል መሠረት ብቻ ይሆናል::

በግልፅ እንደተቀመጠው የድንበር ኮሚሽኑ ከዚህ ውጭ አስታራቂ አማራጭ የማቅረብም፣ የመወሰንም ሥልጣን የለውም:: ይህም (ex. aeguo et bono- a term that means according to what is right and good] የሚል ነበር፡ (ሐ) የኮሚሽኑ ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይኖረው ውሳኔ ይሆናል:: ይህ የድንበር ኮሚሽን በሁለቱም ወገን የቀረቡ ታሪካዊና ሕጋዊ ሰነዶች፣ የቅኝ ግዛት የድንበር ውሎችና ካርታዎችን መርምሮ ለሁለቱ ወገን ላቀረባቸው ጥያቄዎች ምላሽ ከተቀበለ በኋላ (የአልጀርስ ስምምነቱ ከተፈረመ ሁለት ዓመታት በኋላ) የሁለቱም መንግሥታት ባለሥልጣኖች በተገኙበት በሄግ፣ ኔዘርላንድስ ሚያዝያ 13 2002 (ኤ.ኤ.አ) ውሳኔ ሰጠ::

**3.** የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔውን ለመስጠት በተሰየመበት ዕለት የኢትዮጵያ መንግሥትን በመወከል ከፍተኛውን ኃላፊነት ወስደው ጉዳዩን ለሁለት ዓመት ይመሩና ይከራከሩ የነበሩት አቶ ስዩም መስፍን ግን በቦታው አልነበሩም:: በእሳቸው ምትክ የኢትዮጵያን መንግሥት የወከሉት አምባሳደር ፍስሃ ይመር (በወቅቱ በስዊዘርላን የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበሩት) ናቸው:: የድንበር ኮሚሽኑና ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው የውጭ ሃገራት ዲፕሎማቶች በወቅቱ የገረማቸው ኢትዮጵያን በመወከል የበላይ ኃላፊ ሆነው ጉዳዩን የመሩት አቶ ስዩም መስፍን ለምን እንዳልተገኙ ነበር:: በርግጥም ጉዳዩ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው እንጂ ለአምባሳደር የሚተውም ጉዳይ አልነበረም:: የ80 ሺህ ኢትዮጵያዊያንን ሕይወት የቀጠፈ፣ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ከመኖሪያው ያፈናቀለና ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ያስከተለ ጦርነት መሆኑ እየታወቀ በቦታው አለመገኘታቸው አነጋጋሪ ጉዳይ ሆኖ 18 ዓመታት አስቆጥሯል:: ስለሆነም አቶ ስዩም መስፍን ሃቁን ለኢትዮጵያ ሕዝብ መግለጽ ይጠበቅባቸዋል::

**4.** የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔውን ባስታወቀ ሁለት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አቶ ስዩም የተሰጠውን ባለ 125 ገፅ ውሳኔ ሳያነቡና ሳይመረምሩ፣ እንዲሁም በስፍራው ተገኝተው ውሳኔው ካደመጡት አምባሳደር ፍስሃ ይመር ማብራሪያ ሳይጠይቁ አዲስ አበባ ላይ ጋዜጠኞች ጠርተው "ባድመ ለኛ ተወሰነ" ሲሉ በሰበር ዜና ለኢትዮጵያ ሕዝብ የደስታ መግለጫ አስተላለፉ:: የሀገርና የውጭ አገር ጋዜጠኞች በተገኙበት ጋዜጣዊ መግለጫ ስዩም መስፍን በድንፋታና ፉከራ "በባድመ ጉዳይ የሕግ የበላይነት የጫካ ሕግን አሸንፏል፣ የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊና ፍትሐዊ ነው:: በግንቦት 1998 ኤርትራ ይገባኛል በማለት የወረረችው ባድመና አካባቢው በድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ መሠረት የኢትዮጵያ መሆኑን ተረጋግጧል... እኛ ውሳኔውን ሙሉ በሙሉ ተቀበለነዋል ፤ የዓለም ሕብረተሰብም ኤርትራ ውሳኔውን እንድትቀበል ማስገደድ አለበት" አሉ::

በተጨማሪ "የኢትዮጵያ መንግሥት ይገባኛል ያላቸውን ሁሉም ቦታዎች በውሳኔው መሠረት አግኝተናል" ሲሉ በቦታው የተገኙት የሃገር ውስጥና የውጭ ጋዜጠኞች እንኳን ደስ አሎት በማለት ሞቅ ያለ ጭብጨባ አደረጉላቸው:: በዐሥር ሺህ የሚቆጠሩ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን መስቀል አደባባይ አስወጥተው አስጨፈሩ:: በዕለቱ በኤርትራ በኩል ግን ስለ ድንበር ኮሚሽን ውሳኔ የተሰጠ መግለጫ አልነበረም:: ከሁለት ቀን በኋላ ግን የኤርትራ መንግሥት ዝርዝር ውሳኔውንና የተጠቀሰውን (reference points, coordinates) ካገናዘበና የካርታ እውቀት ያላቸው ኤክስፐርቶች ጋር ረጅም ጊዜ የፈጀ ውይይት ካደረገ በኋላ አጠር ያለ መግለጫ አወጣ ይህም "በጉዳዩ በአሸናፊነት የተወጣው የኤርትራ ሕዝብ ነው" የሚል ነበር::

**5.** እስካሁን ይፋ ያልተደረገው የአቶ ስዩም መስፍን መግለጫ ምሥጢር በወቅቱ ውሳኔው በዘሄግ ኔዘርላንድ ሲሰጥ በቦታው ከነበረ የአፍሪካ ሕብረት ተወካይ ጋር የተያያዘ ነው:: ይህ የአፍሪካ ሕብረት ተወካይ ኮሚሽኑ ውሳኔውን ባስታወቀ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተሰጠውን ውሳኔ በጥሞና ሳያጤን አዲስ አበባ ወደሚገኘው የሕብረቱ ዋና ጽ/ቤት ለአለቃው አስቸኳይ መልዕክት በኢሜይል አደረሰ:: በግንቦት 13 ቀን 2002 (ኤ.አ.አ) ከዘሄግ ኔዘርላንድ ወደ አዲስ አበባ የተላከው ኢሜይል "የተወሰነው ድንበር መስመር ኤርትራ ይገባኛል እንዳለችው ነው::

ይህም ሁለቱን አገሮች ከሱዳን ጋር የሚያዋስነው ድንበር ተነስቶ የመረብን ወንዝ ተከትሎ ወደ ስቲት ይዘልቃል (አመልካች ነጥብ 6) ከዚያም በቀጥታ ወደ ማይ አንበሳ ይደርሳል (አመልካች ነጥብ 9) ይህ የቅኝ ግዛት ድንበርን የሚያረጋግጥ ሲሆን ኢትዮጵያ ባድመ ተረጋግጦላታል" የሚል ነበር:: የኢሜይል መልዕክቱን ያገኙት የአፍሪካ ሕብረት ባለሥልጣን ባድመ ለኢትዮጵያ ተወሰነ የሚለውን እንዳዩ ነገሩን ረጋ ብለው ሳያጣሩና ሳያጤኑ ለአቶ ▶

ስዩም መስፍን የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት ያስተላልፋሉ። የሚደንቀው የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ባለ 125 ገፅ (ብዙ ካርታዎችንና ሰነዶችን ያጠቃለለ) ትልቅ ሪፖርት ሲሆን የአፍሪካ ሕብረቱ ታዛቢ ውሳኔውን ከካርታ ጋር ሳያገናዘብ በችኮላ ለመላክ ምን አስገደደው? የሚል ጥያቄ ማንሳቱም ተገቢ ይመስለኛል።

የድርጅቱ ከፍተኛ ባለሥልጣን በጉዳዩ ላይ ገለልተኛ መሆን ሲጠበቅበት የተዛባ መረጃ መላኩ የአፍሪካ ሕብረትን የሚያስወቅስና በጣም የሚያሳፍርም ተግባር ነው።

**6.** አቶ ሥዩም መስፍን የተሰጠውን ባለ 125 ገፅ ውሳኔ ሳያነቡና ሳይመረምሩ በተለየም በስፍራው ተገኝተው ውሳኔው ካደመጡት አምባሳደር ፍሰሃ ይመር ማብራሪያ ሳይጠይቁ ተቻኩለው መግለጫ የሰጡትና የተሳሳተ መረጃ ያቀረቡት ከአፍሪካ ሕብረት የተገኘን ያልተጨበጠ መረጃ በመያዝ መሆኑን ከዲፕሎማቲክ ምንጮች አረጋግጩያለሁ። ዕውነታው ይህ ከሆነ ታዲያ አቶ ስዩም መስፍን ያልነበሩበትንና ያልሰሙትን፣ ቢሰሙትም ለመረዳት ግዜ የሚጠይቀውን ውሳኔ በፍጥነት "ባድመ ለኛ ተሰጠ" በማለት አዲስ አበባ ላይ እንዴት መግለጫ ሰጡ? "የጠየቅነውን ብቻ ሳይሆን ያልጠየቅነው ጭምር ተፈረደልን" ብለው የድንበር ኮሚሽኑን ባመስገኑ በሳምንታት ግዜ የድንበር ኮሚሽኑን መውቀስ የዲፕሎማሲያዊ ብቃት ማሳያ ነውን? ይግባኝ የሌለው ውሳኔ ለመቀበል በመሪዎች ደረጃ ስምምነት ከተደረሰ በኋላ የኮሚሽኑን ውሳኔ ላለመቀበል ቅድመ ሁኔታ መደርደርስ ስለ ዓለም አቀፍ ሕግ ግንዛቤ አለኝ ከሚል ዲፕሎማት ይጠበቃልን? ይህም የአቶ ስዩም መስፍን የብቃት ክፍተት መግለጫ ሲሆን ደርጊቱ ኢትዮጵያን ያሳፈረ ስለሆነ በታሪክ ሲዘከር ይኖራል።

**7.** ከጥቂት ቀናት በኋላ ግልጽ እንደሆነው ባድመ የተወሰነው አቶ ስዩም መስፍን እንዳሉት ለኢትዮጵያ ሳይሆን ለኤርትራ መሆኑ ተረጋገጠ። ይሄኔ አቶ ስዩም ይበልጥ ትዝብት ውስጥ የሚጥላቸውንና ዲፕሎማቶችን ጭምር ያስገረመ መግለጫ ሰጡ። መግለጫውም "ፍትሐዊና ሕጋዊ ነው። መሉ በሙሉ ተቀብለናል" ከሚለው አቋማቸው በማፈግፈግ "ውሳኔውን የኢትዮጵያ መንግሥት በመርህ ደረጃ ተቀብሎታል። ነገር ግን ማስተካከያ ማሻሻያ ነጥቦች ያስፈልጋል" የሚል ነበር። ለዚህም ከኤርትራና ከዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ አጥጋቢ መልስ ስላላገኙ ከጥቂት ወራት ቆይታ በኋላ ለድንበር ኮሚሽኑ ረዥም ሃተታ የያዘ አቤቱታ በደብዳቤ አቀረቡ። የድንበር ኮሚሽኑም በጽሁፍ ምላሽ ሰጠ። "የሰጠነው ውሳኔ መሠረት ያደረገው በቅድሚያ በአልጀርስ በተደረገውና በተስማማችሁበት መርህና ለኮሚሽኑ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው" በማለት አቤቱታውን ውድቅ አደረገው።

**8.** በ2003 ጠቅላይ ሚ/ር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ በወቅቱ የተባበሩት መንግሥታት ዋና ፀሐፊ ለነበሩት ኮፊ አናን በላኩት አቤቱታ የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ "የዓለም ሕጎችን የጣስ ኢፍትሐዊና ኃላፊነት የጎደለው" በማለት አጥላልተው የድንበር ጉዳዩ ከድንበር ኮሚሽኑ ውጭ በተባበሩት መንግሥታት እንዲታይና ሌላ አማራጭ እንዲፈልጉለት ተማጸኑ፡፡ በደብዳቤያቸውም "ይህን ኢፍትሐዊ ውሳኔ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት አይቀበለውም" ብለው ግትር አቋም ያዙ። አስገራሚው ነገር ኮፊ አናን የአቶ መለስን አቤቱታ ተቀብለው ከኤርትራው ፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ለመወያየት ወደ አሥመራ ተጓዙ። ዋናው ፀሐፊው ለፕሬዝዳንት ኢሳይያስ ከድንበር ኮሚሽን ውሳኔ ውጪ ሌላ አማራጭ መንገድ ቢፈለግ ይሻላል ብለው ሃሳቡን አቀረቡ።

የኤርትራው ፕሬዝዳንት በመገረም ኮፊ አናን በተገኙበት የሁለቱ አገሮች መሪዎች የአልጀርሱን ስምምነት የተፈራረሙት በድንበር ኮሚሽን የሚወሰነው ይግባኝ የሌለው የመጨረሻ ውሳኔ መሆኑን በማስታወስ ኮፊ አናን ወቀሱ። ያቀረቡት ሃሳብ ተቀባይነት እንደሌለው ገልፀው ስብሰባውም በአጭሩ ተቋረጠ። ኮፊ አናንም በኤርትራ ከ2 ሰዓት በላይ ሳይቆዩ ለመመለስ ተገደዱ። አቶ መለስ ለኮፊ አናን የላኩት ደብዳቤ ስለ ድንበር ኮሚሽኑ ብቃት ማነስ የሚዘረዝር እና ዘለፋም ያዘለ በመሆኑ የድንበር ኮሚሽኑ በጉዳዩ ላይ አጠር ያለ መግለጫ ሰጠ፡ "ሊፈወስ የማይችል ምንም አስጊ ጉዳይ የለም፤ ተፈላጊው ነገር የኢትዮጵያ መንግሥት በአልጀርስ የገባውን ውል በተለይም በድንበር ኮሚሽን የተሰጠውን ብይን የመጨረሻና የማይለወጥ ወሳኔ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል" ሲል አጭር መልዕክት አስተላለፈ።

**9.** የወያኔ ምንም ሕጋዊ መሠረት የሌለው አቤቱታ ተቀባይነት ስላጣና በኮፊ አናን የተሞከረውም በኤርትራ ከፍተኛ ተቃውሞ ስላጋጠመው የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ ለማስቀየር ቀጥለው የተጠቀሙበት ዘዴ የአሜሪካ መንግሥትን ድጋፍ መጠየቅ ነበር፡፡ ወያኔ በአፍሪቃ ቀንድ የአሜሪካ ጉዳይ አስፈፃሚ ለመሆን የተስማማ መሆኑ ይታወቃል። የአሜሪካንን ፍላጎት ለማስፈጸም በሶማልያ ጣልቃ የገባ እና የአሜሪካን የፀረ ሽብርተኝነት ስትራቴጂ ተባባሪ በመሆኑ ይህንኑ ግንኙነት ተጠቅመው የአሜሪካን ድጋፍ በጥብቅ ተማፀኑ።

ለዚህም እንዲረዳ አዲስ ባለ አምስት ነጥቦች "የሰላም ሃሳብ" ለአሜሪካ መንግሥት አቀረቡ። እያይዘው 'የድንበር ውሳኔውን በመርህ ደረጃ ተቀብለነዋል፡ ውሳኔው ማሻሻያ/ ማስተካከያ ቢደረግለት ሙሉ በሙሉ እንቀበላለን" በማለት አሜሪካኖችን ተማጸኑ፡፡ አቶ መለስ "በመርህ ደረጃ ተቀብለናል" (accept in principle) የሚለውን አዲስ ሀረግ የጨመርነው ውሳኔውን ጠቅላላውኑ አንቀበልም ከማለት ይሻላል ብሎ የእንግሊዝ መንግሥት ስለመከረን ነው" ማለታቸው በዊኪሊክስ ተጋልጥዋል።

**10.** በ2006-2007 ሌላ የተፈጸመው ድራማ የአሜሪካ መንግሥት የአፍሪካ ጉዳዮች ምክትል ሚኒስትር ጃንዳይ ፍሬዘር በወያኔ አቤቱታ መሠረት የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ ለማስቀየር ያደረጉት ሙከራ ነበር። ጀንዳይ ፍሪዘር በወቅቱ በተባበሩት መንግሥታት የአሜሪካ አምባሳደር ለነበሩት ጆን ቦልተን ያስተላለፉት ትዕዛዝ በተመለከተ 'Surrender Is Not An Option Defending America at the U.N and Abroad" በተባለው መጽሐፋቸው ጆን ቦልተን እንዲህ አቅርበውታል።

"በፍፁም ምን እንደሆነ ግልጽ ባልሆነና ባልገባኝ ምክንያት የወቅቱ አለቃዬ የነበረችው ጃንዳይ ፍሪዘር በፊት የነበረውን የአሜሪካ መንግሥት አቋም በመቀየር በ2002 የተወሰነውን የድንበር ውሳኔ ስህተት ነበር ብላ ስለደመደመች በየካቲት 2006 ይህን ውሳኔ እንዳስቀይር፡ በዚህም አከራካሪው ድንበር ለኢትዮጵያ እንዲሰጥ እንዳደርግ ትዕዛዝ ሰጠችኝ። እኔ ግን ምን ብዬ ለተባበሩት መንግሥታት ሴኩሪቲ ካውንሰል አባላት እንደማሳምን ስለተቸገርኩ የተባልኩትን አላደረኩም ::(pp 347)

**11.** አቶ ስዩም መስፍንና ወያኔዎች የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ ለማስቀየር ያደረጉት ሙከራ ሁሉ ምንም ውጤት ሊያስገኝ ስላልቻለ በድንበር ኮሚሽኑ ላይ የስድብና ዛቻ ዘመቻ ቀጠሉ። የድንበር ኮሚሽኑ ሲቀመንበር ባወጡት መግለጫ የድንበር ኮሚሽኑ የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ በማስመር "የሁለቱ ሀገሮች የድንበር ውዝግብ በውሳኔው መሠረት በሚያዝያ 13/2002 ተደምድሟል። ምንም እንኳ በድንበሩ ላይ ችካል ባይደረግበትም የድንበር ውሳኔው ለሁለቱም ሀገሮች የፀና ነው።

በውሳኔው እንደተገለፀው ሁለቱ ወገኖች ከተስማሙ ብቻ የሚሆን አንዳንድ ጥቃቅን ማስተካከያ ሊደረግ ይችላል። ከዚህ ውሳኔ ውጪ የሚደረግ ማንኛቸውም ዓይነት ውሳኔ ሕጋዊነት የለውም" በማለት የመጨረሻ መልዕክታችውን አስተላለፉ። የኤርትራ መንግሥት የወሰደው አንድና ግልፅ የሆነ አቋም የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ መቀበል ብቻ መሆኑን አስምሮበት በአቋሙ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ማለት ከአሜሪካ መንግሥት፡ ከተባበሩት መንግሥታት፣ ከአውሮፓ ሕብረትና ከአፍሪካ ሕብረት የገጠመውን ከፍትኛ ጫና በርጋታና በአቋሙ በመፅናት ሊመክተው ችሏል።

**12.** ወያኔ ለ17 ዓመታት የኤርትራና ኢትዮጵያ ሕዝቦች ግንኙነት አደገኛ ደረጃ እንዲደርስ አድርጎ አልፏል። በቁርና ፋኖ በተቀጣጠለው ማዕበላዊ ግፊት ከሥልጣኑ ተባርሮ ከአራት ኪሎ ቤተመንግሥት ወደ መቀሌ የሸሸው ቡድን ችግሩን ጥሎ ሲሄድ፣ የዶ/ር ዐቢይ አሕመድ መንግሥት ያለምንም ማመንታት የድንበር ኮሚሽኑን ይግባኝ የሌለውን ውሳኔ በመቀበል ተንቀሳቀሰ።

በዚሁ ላይ የተመረኮዘ የሰላም ጥሪ ለኤርትራው መሪ አቅርቦ ኤርትራም ለረጅም ጊዜ የታገለችለት አቅዋም አጥጋቢ ምላሽ በማግኘቷ በአጭር ጊዜ አምንታዊ ምላሽ ከፕሬዝዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂ አገኘ። ለዛም የኖቤል ሰላም ኮሚቴው የማይቻል ይመስል የነበረውን በዲፕሎማሲ ብቃትና በልበሙሉነት የሁለቱ አገሮችና ሕዝቦች የሰላም እና ብልጽግና ጎዳና የመረጡትን ዐቢይ አሕመድን ሸለመ። ይህ ታላቅ የሰላም ሽልማት በዲፕሎማሲ ልቆ የመገኘት ሽልማት ነው። የአቶ ስዩምና ወያኔዎች የ17 ዓመታት "የከሸፈ ዲፕሎማሲ ጉዞ" በዶ/ር ዐቢይ የወራት ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ምላሽ አገኘ። የወያኔ መሪዎች በሥልጣን ላይ ብዙ ቆይተው ያልቻሉበትን የዲፕሎማሲ ጥበብ ከሸሹበት መቀሌ ከዶ/ር ዐቢይ የተማሩ ይመስለኛል። ክፋቱ ሥልጣን ከተነጠቁና ካረጁ በኋላ ሆነ እንጂ።

የሕግ የበላይነትንና የድንበር ኮሚሽን ውሳኔን መቀበል አርቆ አሳቢነትንና ልበ ሙሉነትን ይጠይቃል!

...በሰላማዊውና ንፁህ ኤርትራዊያን ላይ የፈፀማችሁትን ግፍ የትግራይ ሕዝብ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ግንዛቤ እንዲያገኝበት በማሰብ የዚህ የጽሁፍ ቅጅ በዶ/ር ደብረጽዮን ገብረሚካኤል በኩል እንዲደርሳችሁ የእሳቸውን ትብብር እጠይቃለሁ...

***ረዘነ ተስፋይ***

***ዋሽንግተን ዲሲ***